
ሊቀ ትጉሃን ወንደሰን ተገኝ
ዋጋ 10:00 ብር


ውሾች አበቡኝ
ዐገቱኒ ከለባት

http://www.andadirgen.blogspot.com/

አንድ አድርገን

ሌሎች ስለተሐድሶ እና መናፍቃን እንቅስቃሴ የተፃፉ መፅሀፍትን ለማውጣት በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡

‹‹የምንፈራው እውነት የለም››




# ውሾች ከበቡኝ

አዘጋጅ

ሊቀ ትጉሃን ወንደሰን ተገኝ

ሚያዝያ 2003

መጽሐፉን ለማከፋፈል ለምትፈልጉ

0911-65-61-46

## መታሰቢያነቱ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በብዙ የአብነት ትምህርት ቤት ተምረው በቤተክርስቲያናችን ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተምረው ግን እንዳልተማሩና እንዳላዋቂ ተደርገው ብግፍ ለተገፉ አገልጋዮች ይሁንልኝ

## ምስጋና

ይህን መፅሐፍ እንድፅፍ በነገሩ ሁሉ ለረዳኝ ለልዑል ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና አምልኮትና ውዳሴ ለእርሱ ይሁን አሜን

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቁርጥ ቀን ልጆች በበዓለ ጥምቀት ጊዜ አስፋልት በማጠብ ጨፌ በመጉዝጉዝ ምንጣፍ በማንጠፍ እንዲሁም በክብረ በዓል ጊዜ ቤተክርስቲያናችንን ዙሪያዋን በአገራችን ባንዲራ በማሸብረቅ ላደረጋችሁ ወንድሞቼና እህቶቼ ይሁንልኝ::

| ማውጫ | ገጽ |
| --- | --- |
| መግቢያ | |
| የተሐድሶ መስራች | 5 |
| የተሐድሶና የኦርቶዶክስ ክርክር | 10 |
| ተሐድሶዎች በኢትዮጵያ | 21 |
| የኦርቶዶክስ መለያ | 27 |
| ዋቢ መጻሕፍት | |

## መግቢያ

«ዐገቱኒ ከለባት»

«ውሾች ከበቡኝ»

አንዲት ሃይማኖት ና አንዲት ጥምቀት የነበረችውን ቅድስት ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ በ451 ዓ.ም ለሁለት በመሰንጠቋ ለሁለት እንድትሰነጠቅ ምክንያት የሆኑትን ቡድኖችን ሊቃውንት አባቶቻችን ጉባኤ ከለባት የውሾች ጉባኤ በማለት የነቢዩን የዳዊትን ቃል ዐገቱኒ ካለባት ውሾት ከበቡኝ የሚለውን መለኮታዊ ቃል መርህ አድርገው ሰይሙት

በዚህ ምክንያት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቃውንት ጉባኤ-ከልባት የውሾች ስብሰብ ብለው ተገንጣዮቹን በመሰየማቸው ምክንያት የዚህችን አጭር መጽሐፍ ርእስ ውሾች ከበቡኝ በማለት የአባቶቼን ፈለግ ተከትዬአለሁ::

# የተሐድሶ መስራች

## «ሥላሴ አትበሉ እግዚአብሔር አትበሉ ኢየሱስ በሉ»

ይህ የማን ትምህርት ነው? የዚህን ሃሳብ ያመነጨው የመጀመሪያው ሰው ተሐድሶው ኤራስምስ ነው ይህ ኤራስሞስ የተባለ ጀርመናዊው ሰው መድኃኔዓለም ክርስቶስ የድንግል ማርያም ልጅ ያስተማረውን ት/ት ከፕሌቶ የግሪክ ፍልስፍና የተቀዳ ነው ብሎም ያምን ነበር:: ይህ ሰው በኢየሱስ ላይ የተሳለቀ በሥላሴ አንድነትና ሦስትነትም ላይ ያሾፈ ሥላሴ አትበሉ ኢየሱስ ብቻ በሉ በማለት የተነሳ የመጀመሪያው ተሐድሶ ነው::

ተሐድሶዎች በአርዮስ መወገዝ ሰዓት መናፍቅ በሐዋርያት ዘመን ቢጽ ሐሳውያን በመባል ሲታወቁ ከማርቲን ሉተር መገንጠል በኋላ ተሐድሶ የሚል መጠሪያን ይዘው በራሳቸው ብቅ ብለዋል:: ከማርቲን ሉተር በኋላ የነበሩት ሁሉ ግለሰቦች አንዱ ከሌላው እኔ እሻላለሁ እኔ ቤተ ክርስቲያንን አስተካክላለሁ አሻሽላለሁ በማለት በየራሳቸው ስም የራሳቸውን ቤተ-ክርስቲያን እየተከሉ የራሳቸውን ዶግማና ቀኖና መሠረት ሃይማኖት እየፈበረኩ በምድራችን ላይ ሰው ሃይማኖት በሃይማኖት እንዲሆን በሽበሽ አድርገውታል:: ከነሱ መነሳት በኋላ አንዲት ሃይማኖቺ የሚለው መለኮታዊ ቃል አባባል ሆኖ እንዲቀር ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል::

ኤራስምሶ በ1466 በፈረንዶች አቆጣጠር በሮተርዳም የተወለደ የቄስ ልጅ ነው:: ኤስድሩስ የቄስ ልጅ መሆኑ ደግሞ ሃይማኖት ላይ እንዲሳለቅ ከፍተኛ ሚና አበርክቶለታል:: የዴስድሩስ ልጅ ኤራስሞስ በሰብአዊ መብት ደረጃ ጥሩ ሰው ነው ተብሎ እንዲነገርት ያደረገ ሰው:: ኤራስሞስ ገለልተኛ ሰው አይደለም የመጀመሪያውን የሉተርን ትምህርት የሚቃወም ነገር ግን የሉተር ተከታይ ነው በታሪክ ምሁራን እንቆቅልሽ የሆነ የኤራስሞስ የህይወት ታሪክ ዛሬም በሀገራችን የሉተርን ትምህርት እቃወማለሁ የሚል ዳሩ ግን የሉተርን ሀሳብ የሚያራምድ የሉተርን መጽሐፍ የሚያቀጥል ነገር ግን ኮፒውን አምጥቶ ለህዝብ የሚቸበችብ ኢትዮጵያዊ ኤራስሞስ የለም ኤራስሞስ ዓላማው በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ቀውስና ብጥብጥ መፍጠር በእጅጉ የሚያስደስተው ሰው ነበር የኤስድሮስ ልጅ የኤራስሞስ ዓላማ ሥጋዊ ጥቅምና ፍላጎትን ማርካት ብቻ ነው ስለሃይማኖት ግድ የለውም ስለ አንዷት ቤተ-ክርስቲያን አይገባውም ኤራስሞስ ሁለት መጻህፍትን አሳተመና ከህዝብ ሊቀላቀል ነው::

ነገሩ እንዲህ ነው:-

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መነሻ በሠራው አዲስ ኪዳን ሦስት ኢላማዎችን ይዞ ብቅ አለ::



1. መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው በሮማውያን አስተሳሰብና የፖለቲካ ፍልስፍና የተጨናነቁትን ሰሜን አውሮፓንና በተለይ ጀርመናውያንን አይዟችሁ ነፃ ትወጣላችሁ የሚል ፖለቲካዊ አንድምታን የያዘ
2. ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሥላሴ አስተምህሮን በመፋቅ ሥላሴ አትበሉ
3. ድንግል ማርያምን እንደ-ነ-መግደላዊት ማርያም የአልአዛር እህት ማርያም ብቻ እንድትሰበክ ነገር ግን ከፍጥረታት በላይ ከጣሪ በታች መሆኗ እንዳይነገር የሚል ጭብጥን የያዘ ነበር::

ኤራስሞስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይ ከአዲስ ኪዳን ውስጥ መሸሻል አለባቸው ያላቸውን ጥቅሶች ሥላሴ የሚለውን ቃልና ስለሥላሴ ሊያስተምሩ ይችላሉ የሚባሉትን ጥቅሶች እየነቀለ በማውጣት ሥላሴ አትበሉ እግዚአብሔር አትበሉ አንድም ሦስትም አትበሉ በማለት የሥላሴን አስተምህሮ በመፋቅ ትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱስ በማለት አሳትመ ይሁን እንጂ የሮማውያን ግዛትና እሳቤ እንዲቀየርላቸው የሚፈልጉት ጀርመናውያን በጭፍን ኤርሳሞስን ለጊዜው ቢቀበሉትም ኤራስሞስ አንድ ተከራካሪና ተሚጋች ከታላቁ ብሪቴን ብቅ አለበት ከታላቁ ብሪትንያ የኤራስሞስን የተሐድሶ ትምህርት ለመቃወም የመጣው የአንድምታው ሊቅና ምሁር ኤድዋድሊ

ይባል ነበር:: ሊ. የኤራስሞስን የተሐድሶ ጽሑፍ በመቃወም ከፍተኛ ክርክርን የያዘ መጽሐፍ በፍጥነት በማሳተም በኤራስሞስ ትምህርት ሰው እንዳይጥረገረግ የበኩሉን ጥሯል ሊ. የኤርስሞስን ትምህርት ብቻ ሳይሆን የኤርስሞስን ግላዊና አስጸያፊ ሕይወት በማገላጥ ኤራስሞስን ማንነት ሰዎች ከፖለቲካና ከሃይማኖት ውጭ እንዲመለከቱትም በማድረግ በመጽሐፍ ውስጥ የኤራስሞስን ግላዊ ህይወት የሚያትት ምዕራፍ አሳትሞበታል::

ይሁን እንጂ በጀርመን ሰብአዊ መብቶች ስም የተቋቋሙት ድርጅቶች ዘንድ በጎ ምላሽ አልገጠመውም ይልቁንም ኤራስሞስ የሮማውያን እሳቤን የፖለቲካ ፍልስፍና ያንገሸገሻቸው ጀርመናዊያን ኤራስሞስን በጭፍን ከነፖለቲካው ተቀበሉት ኤራስሞስ የሮማን ቤተክርስቲያንን በመተቸትና ፖለቲካዊ ሥልጣኑን በመቃወሙ በመጽሐፍ ጀርመናውያንን ግዛትን ጮቤ አስረግጧል::

እነርሱም በተለይ ሰሜናዊው የአውሮፖ ክፍል ልማዳዊ አስተምህሮንና ጎጂ ባህልን ነቅሶ ያሳያንን የሮማ ቤተ-ክርስቲያን እንድትታደስ ያሳየንን ወደ እውነቱ የመራንን ኤራስሞስን እናመሰግናለን ብለው ድጋፋቸውን ገለጹ የአስተሳሰብ ነፃነታቸውን አወጁ ጉዳዩ ሃይማኖት ከሆነ በድምጽ ብልጫና በድጋፍ ሊሆን በፍጹም አይችልም::



እቃወማቸዋለሁ የሚላቸው ሉተራውያንም በተለይ በ1520 የነበረው የሉተራን እንቅስቃሴ መሪ
«ኤራስሞስን የጀርመን ጌጥ» በሚል ቅጽል እንዲመራ አደረገ በርሱ ትምህርት የሉተራን ጽሑፎች ያቀጠሉት መልሰው ኤራስሞስን የጀርመን ጌጥ - አሉት
ምን ማለት ይሆን?

በርግጥ ኤራስሞስ የሠራውን አዲስ ኪዳን ጀርመናውያን ከነበረባቸው ፖለቲካዊ እሳቤ ውጭ ቢመለከቱት ኖሮ ዛሬ በሀገራቸው ያለውን አብያተ-ክርስቲያናት ዘግተው ጭፈራ ቤትና ቡቲክ ባላደረጉት ነበር ሃይማኖትን ከፖለቲካ ለይቶ ማየት ትልቅ ነገር ነው:: ለዚህም. ነው ኤራስሞስ የሰራው ሥራ ምሁራኑንና ትክክለኛ ሃይማኖታችን ሊቀይራቸው ባይችልም የፖለቲካ ይዘትና ቅሬታ ያለባቸውን ምዕመናንን በደካማ ጎናቸው በመግባት በሃይማኖታቸው እነዲጠራጠሩና መጽሐፍ ቅዱስ የሰው እጅ ሥራ እንጂ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም ብለው እንዲያምኑ አድርጓቸዋል::

# የተሐድሶና የኦርቶዶክስ ክርክር

## የሥላሴን ስም የፋቀበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከአዲስ ኪዳን

ለምሳሌ በመጀመሪያይቱ የዮሐንስ መልእክት ላይ ምዕራፍ 5:8 ላይ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦስት ናቸው:: ሦስቱም አንድ ናቸው የሚለውን ቃል ሥላሴ አትበሉ እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው አትበሉ ኢየሱስ ብቻ በሉ በማለት የነበረውን የሥላሴን ስም አስወግዶታል ይህንንም ያደረገበት ምክንያት እርሱ አመሳክሬዋለሁ. ያለው ከግሪክና አዲስ ኪዳን ላይ የእጅ ጽሑፍ ላይ እንደዚህ ዓይነት መርጃ የለም በማለት ይሞግታል የኤራስሞስ የተሐድሶ እንቅስቃሴን የተቃወመው ኤድዋርድ ሊ የአንድምታ መምህሩ ሥላሴ አንድም ሦስትም ናቸው የሚለውን የምስጢር ሥላሴ አስተምህሮ ስለሚያናጋውና ዋነኛ መረጃዎችንም አንድ ብቻ የግሪክኛ የእጅ ጽሁፍ ሳይሆን በርካታ የእጅ ጽሑፎች ስላሉ እነዚያን ሁሉ ማመሳከር እነዚያን አመሳክረን እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው የሚሉ ከሆነ ለአዕምሮ ይከብዳል ብሎ መተው ሳይሆን ፈጣሪ በተገለጸበት መንገድ አንድም ሦስትም ብሎ ማመን ነው ይላል::

ስለዚህ አልገባኝም ብሎ መጠየቅ ይቻላል እንጂ የሥላሴን ስም አትጥሩ ብሎ ማወጁ መፍትሔ አይሆንም ይላል:: የሥላሴን ስም ከአዲስ ኪዳን አትጥሩ ብሎ ማስወገድ ማለት በፈጣሪ ቃል ላይ መጨመርና መቀነስ ነው ይህ ደግሞ በፍጹም ሊሆን



አይችልም ሲል ኤድዋርድ ሊ. የአንድምታው መምህር ይሞግታል::የዚህን የኤራስሞስን አስተምህሮ ሰንቀው የሚነሱ ሰባኪዎችንም ሆነ መንገደኞችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታወግዛለች የምስጢረ ሥላሴ አስተምህሮ ያልገባቸው ለዚህ ለተጠቀሰው መልስ ለኤሪስሞስ የሰለስቱ ምእት የእነ ኢትናቴዎስን የነዲዮስቆሮስ ምላሽ ከበቂው በላይ ነው ይህን የማይቀበል ከሆነ ግን እርሱም ሆኑ ተከታዮቹ በሰለስቱ ምእት ውግዘት ይወገዛሉ ከቤተ ክርስቲያንም ተለይተው ይወጣሉ

እግዚአብሔር አንድ ነው

እግዚአብሔር አብ

እግዚአብሔር ወልድ

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንላለን

ሦስት እግዚአብሔር ማለታችን ግን አይደለም

በስም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብለን ሦስትነቱን ለመግለጽ እንጂ እግዚአብሔር አብ በሁሉ ላይ በሁሉም በምልአት ያለ ነው እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስም በሁሉ ላይ በሁሉም በምልአት ያለ ነው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ከአብ የሠረፀ አንድ አካል ነው ::

እግዚአብሔር አንድ ነው የማትከፈል የማትፈልስ መንግሥትም አንዲት ናት ከሥላሴ ምንም ምን ፍጡር ደኅራዊ የለም በእነርሱ ዘንድ አንዱ ለአንዱ መገዛት የለም:: ጉባኤ የቆመለት ቤተ-

ክርስቲያናችን የተቀበለችው ሐዋርያት ያስተማሩት እውነተኛ ትምህርት ይህ ነው::

ይህንንም ትምህርት መሠረት በማድረግ ሥላሴ አትበሉ እግዚአብሔር አትበሉ የሚሉትን ተሐድሶዎች እናወግዛለን የወልድ መገኘት ከማርያም ወዲህ ነው ብለው የሚያስቡትን የሥለሴን አስተምህሮ የሚያናጉትን የፎጢኖስ መንፈስ ያደረባቸው የኤራስሞስ አለማወቅ የተጸናወታቸውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታወግዛለች::

እኛ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከድንግል ቢወለድም እግዚአብብር እንደሚባልና እግዚአብሔር እንደሆነ እንመሰክራለን ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ በአምላክነቱ) ከአብ ጋር ያልኖረበት ዘመን ቀን የለም በዘመኑ በቀኑ ሁሉ አለና እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆነ ስንል እግዚአብሔርነቱ ቀረበት ማለታችን አይደለም እርሱ እግዚአብሔር ነው ለምሳሌ አዳም ኖህ አብርሃም ሙሴ ኢያሱ ሳሙኤል ዳዊት ኢሳይያስ ኤርምያስ የቀሩት ሁሉ ነቢያትም ናቸው ኢየሱስ ክርርቶስ ግን ሰው ሲሆን አምላክ እግዚአብሔር ነው እርሱ ብሉይንና ሐዲስን የሠራ አምላክ እግዚአብሔር እርሱ ነው::

ሐዋርያት ለሰበሰቡት ለቤተ-ክርስቲያን ልጆች ይልቁንም በውስጧ ለሚኖሩ የተዋሕዶ ልጆች ሕይወታቸው ይህ ነው እንዲህ አምነው ይኖሩ ዘንድ ለልጆቻቸው ሊያስተምሩ ይገባቸዋል እንዲህ ካላደረጉ ክርስቲያን ነን እንድናለን አይበሉ::



ለምሳሌ - ይላል ኤድዋርድ ሊ.ስለ መጽሐፍ አተረጓጎም ሲናገር ሐዋርያው ናትናኤል በበለስ ስር ተቀምጦ ስለመታየቱ የአንድምታ ሊቃውን የተለያየ አይነት አገላለጽ አስቀምጠዋል አምስት አይነት ትርጓሜዎች አሉ ይላል

ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ናትናኤልን ወደርሱ ሲመጣ አየውና በውነት ክደትና ተንኮል የሌለበት እሥራኤላዊ እነሆ ብሎ ስለርሱ መሠከረ ናትናኤልም ከወዴት ታውቀኛለህ አለው ጌታም ፊሊጶስ ሳይጠራህ ከበለስስ በታች ሳለህ አየሁህ ዮሐ 1÷48

1. ንጉሥ ሔሮድስ ሕፃናትን በገደለ ጊዜ የናትናኤል እናት በንብ ቀፎ አድርጋ ከበለስ ሥር ሰውራው ነበርና
2. ሰው ገድሎ አስቀብሮ ሰው ሳያየው ከበለስ ስር ለብዙ ጊዜ ተሰውሮ ነበርና
3. እጅግ ሀብታም ስለሆነ ከበለስ ማሳ መሃል እየተዝናና ወይፈኖችን ሲያስትን ፈረስናና በቅሎን ሲያስገራ ይውላልና
4. ኦሪትን የተማረ ሊቅ በመሆኑ ከበለስ ስር በዓቱን ሰርቶ የተቀጠረው ሱባኤ የተነገረው ትንቢት ደረሰ እያለ ይጠባበቅ ነበርና

5. የበስ ዛፍ ሰፊና ቅጠሎቹም የተንዥረገቡ በመሆናቸው የናትናኤልን ሀጢአት ለመግለጽ እነዚህን ሁሉ ሐተታዎች ያጠቃልላል ይላል::

ከነዚህ ትርጓሜዎች ሁሉም ትክክል ናቸው ነገር ግን እንዴት ሁሉም ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ? ብሎ ኤራስሞስ ሲጠይቅና ወደ መገኛ ቋንቋው በግሪክኛ ወደተጻፈው አያስኬደንም ቢሄድ የሚያገኘው የናትናኤልን በበለስ ስር መቀመጥ ብቻ ነው ስለሆነ የተቀመጠበትን ምክንያት ባለማወቅ ከመጨነቅ ብሎ ከበለስ ሥር የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መቀየር በፍጹም አይፈቀድለትም:: የተሐድሶው መስራች ኤራስሞስም ግንየአንድምታ ፍቺ የሚዘገቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ይፋቁ ይወገዱ የሚል አቋም ነበረው::

በዚህ አቋሙም ከላይ ከተደረደሩት ምክንያቶች የትኛው ትክክለኛ እንዲሆነ ለማወቅ ያስቸግራል ምን አልባት ማስረጃው ወይም ምንጩ አልተጠቀሰም እንጂ እያንዳንዱን ምክንያት የተለያዩ ሊቃውንት ተናግረው በኋላ አንድ አስተጋባኢ ሁሉንም ሰብስቦ በአንድነት ያስቀመጣቸው ይመስላል ስለዚህ በመጀመሪያ በተጻፈበት ቋንቋ ፊደላዊ ትርጉሙን ማየትና መመርመር ያስፈልጋል መጽሐፍ ቅዱስን ምእመናን እንዲጠራጠሩት ያደርጋል



# የሉተርና የኤራስሞስ ግጭት

የሉተርና የኤራስሞስ ግጭት የሃይማኖት አስተምህሮ ወይስ ሌላ ሉተርና ኤራስሞስ - ሃይማኖታቸው አንድ ነው ሉተር ከሮማ ቤተ-ክርስቲያን መሻሻል አለባቸው የሚላቸውን ነጥቦች ይዞ ተገነጠለ የሉተር ዘመን የነበረው ኤራስሞስም የሉተር ሃሳብ አራማጅ ቢሆንም በአንድ ሥጋዊ ጉዳይ ከሉተር ጋር ተፋጠጡ::

ኤራስሞስ በ1511 ወደ ኢንግላንድ ለሁለተኛ ጊዜ አቅንቷል ሁለት ጊዜ ሰላምታ አንዱ ለነገር ነው እንዲሉ ኤራስሞስ በዚያ ሲሄድ የካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ የአካዳሚክ አባል ሆኖ ተሾመ በዚያም ታዲያ አንዲት ታዋቂ ሴት ማርጋሬት የምትባል ነበረች ይህቺ ሴት ሉተር ቆቡን የጣለባትና ከሮማ ቤተ-ክርስቲያን የተገነጠለባት ምክንያቱ ኤራስሞስም ሥላሴ አትበሉ በማለት<u>የሥላሴን ስም የፋቀበት</u> ምክንያቱ ስትሆን በእውቀቱ ተጠግቼ አፈቀርኳት ያላት ናት በዚህች ሴት ፍቅር ሁለቱ የተሐድሶ ዘመን ሰዎች ተፋጠጡ ተጣሉ::

የዚህ የሥጋዊ ፍላጎታቸው ግጭት ቤተ-ክርስቲያን ሥርዓቷን ማስተካከል እንደነሱ አስተሳሰብ 1 ሚስት ለሁለት ትሁን አይነት ህግ እንዲደነገግላቸው ፈለጉ ይህ ፈጣሪ የሰጠው ዓይነት ነው እያሉ በሃይማኖት ካባ ሥጋዊ ምኞታቸውን ለማስፈጸም ደፋ ቀና ይሉ ጀመር::

እነዚህ ሁለት ሰዎችና የአንድምታውን ሊቅ ታሪክ እንደተመለከትነው ሉተርና ኤራስሞስን የሚያጋጫቸው የፀባቸው መነሻ ሃይማማታዊ ፍቅር ፈሪሀ እግዚአብሔር ሳይሆን ማርጋሬት የተባለችው ጀርመናዊት ውብ ሴት ፍቅር አስክሮአቸው እንደሆነ በቋንቋቸው የተጻፉት መጻሕፍት ያጋልጧቸዋል የብሪትንያው ቄስ የአንደምታው ሊቅ ኤድዋርድ ሊ. ግን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው የሃይማኖቱ እውነተኛ አርበኛና ጠበቃ እንደነበር ከሙግቱ ማወቅ ይቻላል::

ውድ አንባብያን ዛሬ የኤራስሞስንና የተሐድሶ ንቅናቄና አላማ ተከትሎ ስንቱ በየአውደምህረቱ ምዕመናንን ግራ እያጋባ እንደሆነ ሳታውቁት አትቀሩም በርግጥ ካባው የኦርቶዶክስ የሚመስል ድምጹ ግን የተሐድሶው የኤራስሞስ መልእክትና አላማን ያዘለ ሰባኪ አለ መሰላችሁ የለበሰው ሰናፊል ቀሚስ እንኳ ጥርት ያለ የኦርቶዶክስ ስፌትና አሠራር አይደለም የሌሎች ነው::

ከኤራስሞስ ታሪክ ማወቅ እንደሚቻለው ተሐድሶ እንዲሆን ያበቃው በትምህርት ችሎታው ኤራስሞስ የተባለው የተሐድሶ መሪ በመጀመሪያው ቅዱስ አገስጢኖስ ከሚባል ገዳም ገባ ውሎ ሳያድር የገዳሙ የአኗኗር ስርዓት ከባድና ሊወጣው እንደማይችል ስለገባው አልፈልግም የገዳም ስርዓት ካልታደሰ ካልተሻሻለ ገዳም አያስፈልግም አለ እንደ አጋጣሚ ባፉ ቅልጥፍና የካምፕሪጁ ጳጳስ ጠራውና ሥራ-ና-ነጻ- የትምህርት እድል



በመስጠት ፓሪስ ውስጥ በሚገኘው በሞንቲያጎ ዩኒቨርስቲ እንዲማር ፈቀደለት ይሁንእንጂ በዚያም የትምህርት ቤቱን ሥርዓትናደንብ ባለማክበሩ ከትምህርት ቤቱ ተባረረ በዚህን ጊዜ ቁጭቱንና ስንፍናውን ለመደበቅ ገዳም አያስፈልግም ጳጳስ የለም ነፃነት ያስፈልገናል በሚል የፖለቲካ ቅስቀሳው ሥላሴን የሚቃወም አዲስ ኪዳን እንዳሳተመ ከቤተ-ክርስቲያኗ ወጣ::

የግጥምጥምና የታሪክ ራሱን መድገምም በሀገራችን ይታያል የኤራስሞስን ቦታ ተክቶ የሚንቀሳቀሰው የተሐድሶው ፊት አውራሪ ከሰንበት ት/ቤት እንኳን ሊያስገባው የሚያስችል ዕውቀት ባይኖረውም እንደ ኤራስሞስ ባገኘው የትምህርት ዕድል መጠቀም የሚያስችል በቂ ችሎታ ስላጠረው የትምህርት ቤቱን ሥርዓትና ደንብ ማቃወስ ጀምሯል::

በዚህም አካሄዱ ስንፍናውን መሸፈን ሲል ብቻ በዋናነት «ሲኖዶስ የለም» በማለቱ ከትምህርት ገበታው ተባረረ ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ ወደ ዋና አላማቸው የገቡት:: በስብከቶቻቸውን በመጣጥፎቻቸው የተሐድሶውን የኤራስሞስን ፈለግ በመከተል

- ሥላሴ አትበሉ
- ለጠላቶቼ (ለአጋንንቱ) ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ
- ስለ እመቤታችን ስሟን መጥራት ባለመፈለግ ከአንዲት ሰማያዊት ተወለደ የሚል የንቀት ዐ-ነገርና ኦርቶዶክሳዊ ያልሆነ አገላለጽ በመጠቀም

የቅድስት ቤተ-ክርስቲያንን አስተምህሮ በመናድ የግል ጥቅማቸውን የሚያራምዱ ዛሬም በየጉያችን አይጠፉም ምን አልባትም ብቻ ሳይሆን በእርገጠኝነት የነዚህ አላማዎች የመጨረሻ ግባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ወደ ጭፈራ ቤት እንዲቀየሩ ለማድረግ ነው::

ይህ ደግሞ በዓለማችን ያሉ የስለላ ድርጅቶች ዋና አላማ ቢሆንም በኢትዮጵያ ግን የተሳካላቸው አይመስልም እግዚአብሔርን እየጠሩ በመጨረሻ ሰይጣንን ማመስገን አብያተ ክርስቲያናትን ወደ መሸታ ቤት መቀየር ምንአልባት ተሐድሶው በተወለደባትና ባደገባት አውሮፓ ተሳክቶ ሊሆን ይችላል እንጂ በሀገራችን በአንድ ልደታ በሁለት ዮሐንስ እየተባለ ከወር እስከ ወር ከአመት እስከ አመት የድንግል ማርያም ስም አማላጅነት የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት በሚሰበክባት ቅድስት ሀገር ግን የተሐድሶ ሴራ ይከናወናልል ብሎ መልፋት ውጤቱ መልፋት ብቻ ሆኖ ይቀራል::

እስኪ አንባብያን ከታላቁ መጽሐፍ አንድ ታሪክ- ላስታውሳችሁ ተሐድሶውን ከኦርቶዶክስ የምንለይበት አካሄድ ይሆንላችኂል:: ዛሬ በየአውደ ምህረቱ ከባው የተዋህደ - ድምጹ የተሐድሶ ከባው የኦርቶዶክስ ድምጽ የኤራስሞስ መነሻው ኢየሱስ መድረሻው ዲያብሎስ የሆነ ሰባኪ ስንት አለ መሰላችሁ:: የይስሐቅ ልጆች የኤሳውና የያዕቆብ ታሪክ ደጋግማችሁ አንብቡት ስታነቡት ይስሐቅ በስተርጅናው ከመጀመሪያ ልጁ ከኤሳው አደን



ምግብ መብላት ፈለገ ይህንን ያወቀው ያዕቆብ ግን የውሸቱን የኤሳውን ልብስ ለብሶ ከእናቱ ጋር ተማክሮ ኤሳው ነኝ ብሎ ወደ አባቱ ቀረበ:: አባቱ ይስሐቅ በስተርጅና አይኑ ፈዞ ነበርና ልጆቹን የሚለያቸው በድምጽና በዳሰሳ ነበር ኤሳውን መስሎ የመጣው ያዕቆብም ወደ አባቱ ቀርቦ አባዬ ይህው ነፍስህ ያመረችውን ምግብ ከአደን ይዤልህ ቀርብኩ አለ::

አባቱም አንተ ማነህ? አለው ያዕቆብም በውሸት ኤሳው ነኝ አለ እስኪ ቀረብ በለኝና ልዳስህ አለው ቀርቦው ዳሰሰው ሲዳስሰው ገላው እንደ ኤሳው ፀጉራም ሆኗል አለባበሱም የኤሳውን ሆኗል::

አባቱ ይስሐቅም ድምጽህ የያዕቆብ ልብስህና ሰውነትህ ግን የኤሳውን ይመስላል አለው:: ዛሬም በእናት ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ጥቅም ውበት ማንነት ለመንጠቅና ሳይጠራ ተጠርቼአለሁ መንፈስ ቅዱስ ላከኝ አዘዘኝ በማለት የተሐድሶዎችን የስብከት ዘዴ በመቃኘት በቅድስት ቤተ- ክርስቲያን አውደ ምህረት የሚያቀረሸው ስንቱ ነው መቼም እንዳይስሓቅ አርጅተን ሳይሆን በስራ ብዛትና በተለያየ የኑሮ ውጣ ውረድ ደንዝዘን የሰበከውን ድምጽ የተሐድሶ መሆኑን ብንለየውም አለባበሱና ሰው ሰራሽ ትህትናው ግን ግራ የሚያገባና ለውሳኔ የሚያስቸግረን ስንቱ ተሐድሶ በየ አውደ ምህረቱ አለ መሰላችሁ? አንድ ቀን ማታለል ይቻላል ሁል ጊዜ ግን ማታለል አይቻልም:: ያዕቆብ ኤሳውን መስሎ ያውም እየታወቀበት ኤሳው

ነኝ በማለት አባቱን ከእግሩ ስር ወድቆ አታልሎታል:: ይሁን እንጂ የዘራውን ክህደት መልሶ አጭዶ ከምሮ ወቅቶ ተመግቦታል::

እርሱ አባቱን በስተርጅና እንዳታለለ ሁሉ እርሱንም በስተርጅናው የራሱ ልጆች ልጅህ ዮሴፍ ሞተ ብለው በዮሴፍ የውሸት ሞት አሳዝነው ሞቱን በስተርጅና አፍጥነውበታል:: እግዚአብሔር እራሱ የቤተ-ክርስቲያን አምላክ እንዲህ እጅ በእጅ ይበቀላል::



## ተሐድሶዎች በኢትዮጵያ

ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ እስከ 451 ዓ.ም ድረስ አንዲት የነበረችው ቤተ ክርስቲያንና ትምህርቷ በስልጣንና በጥቅም ጥማት የተነሳ ለሁለት ስትሰነጠቅ ለቀጥተኛዋና ለትክክለኛዋ ሃይማኖት በእናቱ ኢትዮጵያዊ የሆነው ዲዮስቆሮስ የጋግራን ደሴት ውስጥ በእሥራት አሰልፎ ለዚህች ትክክለኛ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ጺጉሩን ተላጨ ጺሙን ተነጨ ጥርሱን አረገፉት እርሱ አስቅድሞ አወገዛቸው እነርሱ በእምቢተኛነት አስገደሉት::መጽሐፉ ከ451 የተጀመረውን መለያየት በጥቂቱ ተስዳስሳለች የተዋሕዶ አርበኛው የዲዮስቆሮስ ሞት ምክንያት የሆነው 451 ዓ.ም ጥቅምት 5 ቀን በኤልቄደን መንደር በተደረገው በሮማውያን ሴራ የተቀነባበረውን ምክንያት ቤተ-ክርስቲያን ለሁለት ተከፈለች ምስራቅና ምዕራብ ተባለ::

በድጋሚ ምዕራቦች ደግሞ ተከፈሉ ሮማውያኑ አዲስ ይሻሻል የሚሉት አስተምህሮ ይዘው ብቅ አሉ:: ማርያም ኃይል አረማዊት ናት መንፈስ-ቅዱስም ከአብና ከወልድ ይሰርጻል አሉና ከግሪኮቹ ሮማውያን ተለዩ

ከሮማውያን ደግሞ የፍራንሲስካን-የምንኩስና አርማ ተከታይ የሆነና የምሥራቅ ጀርመን ተወላጅ የሆነው ያልተሰበና ያልተጠበቀው ማርቲ ሉተሮ የተባለው መነኩሴ በ1517 ዓ.ም 95

ነጥቦችን የያዘ ጽሑፍ በማውጣት አዲሱን የሮም ሃይማኖት ተቃወመ የቤተ-ክርስቲያን አስተዳደ መሻሻል አለበት አለ::

ከዚህ በኂላ የነበሩት ሁሉ አንዱ ከሌላው ሲለይ ሙሉ በሙሉ አንቃወመም ዳሩ ግን ቤተ-ክርስቲያን መሻሻል አለባት እያሉ በየራሳቸውው ስም ቤተ-ክርስቲያን እየመሰረቱ የግላቸውን አዳዲስ የሃይማኖት ዶግማ እየፈጠሩ ዳጎስ ያለ የገንዘብ አቅም ካላቸው ከቤተ-ክርስቲያን በመገንጠል የተሐድሶውን እንቅስቃሴ ያራምዳሉ

የተሐድሶ ቡድኖች ወደ ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ -ወቅት ገብተዋል ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮያ የገቡት የተሐድሶ ቡድኖች ምንኩስናንና ገዳማዊ ሕይወትን የሚቀመሙ መዳን በእምነትና በምግባር ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው የሚሉ 81 የቅዱሳት መጸሕፍት ይዘት የማይቀበሉ የቅድስት ድንግል ማርያምን አማላጅነት የማይቀበሉና የካህናትን ሥልጣን ክህነትን የሚቃወሙ ነበሩ ይህንን አስተምህሮ ወደ ኢትዮጵያ ይዞ የገባው ጴጥሮስ ሄይሊንግ የተባለ ጀርመናዊ ሲሆን ሐኪም ስለነበረ በወቅቱ በቤተ-መንግሥት ተቀባይነትን አግኝቷል መጸሕፍትን ወደአማርኛ ልተርጉም እያለ ሲያምታ ኖሮአል ይህ የተሐድሶ መሪ ጴጥሮስ ሃይሊንግ በ1652 ዓ.ም ወደ ሀገሩ ሲመለስ በመንገድ በቱርኮች ተገድሏል::

ሳሙኤል ጎባትና ክርስቲያን ከግለር እነዚህ ሁለት የተሐድሶ አራማጆች በ1830 ዓ.ም ወደኢትዮጵያ ገብተዋል:: ሳሙኤል



ጎባት ለ6 ዓመታት በኢትዮጵያ ኖሮ ወደ ሀገሩ ሲመለስ በመንገድ በቱርኮች ተገድሏል ክርስቲያን ከግለር በአድዋ ዙሪያ የዱር እንስሳ ሲያድን የራሱ መሳርያ ባርቆ ገድሎታል:: ሳሙኤል ጎባት የስዊዝ ተወላጅ ሲሆን እነዚህን የተሐድሶ ቡድኖች ወደ ኢትዮጵያ የላካቸው በእንግሊዝ ሀገር ተቋቁሞ የነበረው ቸርች ሚሽነር ሶሳይቲ የተባለው ድርጅት ነበር:: ዛሬም ድረስ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ታሪክ ለማዳከም የቅዱስ ያሬድን ዜማ ለማጥፋት የሊቃውንቱን ቅኔ ለመበረዝ የተዋሕዶን እምነት ለማናጋት በእንግሊዝ ሀገር ዛሬም ድረስ ተሐድሶውያንን ወደ ኢትዮጵያ እየላከ የሚያበጣብጥ በሃይማማት ስም የተደራጀ የሰይጣን መልእክተኛ አለ እኛ የቅድስት ቤተ-ክርስቲያን የተዋሕዶ ልጆች ግን ይህቺን ንጽህትና ቅድስት የተዋሕዶ እምነት አትናቴዎስ አርዮስን የረታበት ቅዱስ ቄርሎስ ተዋሕዶዋን ያብራራለት ሃይማማትን ጠብቀን እስከሞት ድረስ የታመንን እንሆናለን::

በተለይ አሁን አሁን የምናየው የሃይማኖት መነቃቃት ወጣቱ ትውልድ የቅድስት ቤተ-ክርስቲያኑን አስተምህሮ ባህልና ትውፊት ለመጠበቅ በንግሥ በዐላት ላይ ሳርና ቄጤማ እየጎዘጎዘ አስፓልት እያጠበ በዝማሬ ታቦቱን አጅቦ እግዚአብሔርን በማያመልክበት የድንግል ማርያምን አማላጅነት በሚማፀንበትና በሚመሰክርበት ወቅት ተሐድሶውያን መነሳታቸው በእጅጉ

ድፍረትና አታውቁም ማለት መስሎ በወጣቱ ላይ እንደመሳለቅ ይቆጠራል::

እጣን እያሸተትን ስናስቀድስ ያደግነው የጻድቃን የሰማዕታት የቅዱሳን መላእክትን ዝክር ዳቦ እየደፋን ንፍሮ እየቀቀልን ለተራቡት በማብላት ለተጠሙት በማጠጣት የምንዘክረው ሃይማኖታችን የቤተ-ክርስቲያናችን አስተምህሮ ስለሆነ እንጂ ዘመናዊነት ሳይገባን ቀርቶ አይደለም::

አንዳንዶች ያወቁ የመሰላቸው ነገር ግን የታወቁ ሰዎች ይህን አድራጎታችን ሲተቹት ይፈልጋሉ አይድንም ከንቱ ልፋት ዝም ብሎ ንፍሮ መቀቀል ጉልባን ማገንፋት ብለው ሲተቹንና ሊሰድቡን ይሞክራሉ:: ዳሩ ግን መቼም የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ትምህርቷ መብረዝና ምዕመናኖቿ ማዳከም አይቻላቸው በተለይ ድንግል ማርያያ ስሟ በማይጠራበት ሁኔታ ስለ ተዋሕዶ ትምህርት መናገር ኦርቶዶክሶች ነን ቢሉን አንቀበላቸውም በኢትዮጵያ ያለን ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ ገና ስንወለድ ማርያም እየተባለ የድንግል ማርያምን ስም እየሰማን እያዳመጥን ተወለድን የድንግል እናታችንን ስም የሰማነው ገና በመኖቿው ወደዚህች ምድር ስንቀላቀል ነው:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የተዋሕዶ ትምህርት መነሻዋና መድረሻዋ ድንግል ማርያያ ናት:: ከእርሷ የተወለደው አምላክ ሥጋ ለብሶ ሁላችንንም ሊያድነን በመስቀል ተሰቅሏልና:: ስለዚህ ቅድስት



ድንግል ማርያም የሰማይም የምድርም ንግሥታችን እማላጃችን ብለን ልንመሰክር ትልቅ ድፍረት አለን:: የተሐድሶዎችን አላማ በእጅጉ ጠንቅቀን ልንረዳ ይገባናል ተሐድሶዎች በተለይ ነጮቹ በሀገራቸው ትምህርተ ሃይማኖት እየጠፋ የጸሎት ቤታቸው ተዘግቶ ሱቅና የቲአትር ቤት እየሆነ በሀገራቸው አምልኮተ ሰይጣን እየተፈጸመ ወጣት ትውልዳቸውም በሥነ ምግባሩ መረን እየሔደ ሳለ ወደ ሀገራችን ወንጌል እናስተምራለን ብለው መምጣታቸውና ገንዘብ የጠማቸውና ሃይማኖታቸውና ለኢትዮጵያዊነታቸው ግድ የሌላቸውን አልባሌ ሰባኪ ተብዬዎች እንኳን ለማስተማር ተአምር ለመመስከር ብቃት የሌላቸውን የራሳቸውን ዜጎች እየመለመሉ በየቤተ ክርስቲያናችን መላካቸው የኦርቶዶክስን ህልውና የተዋሕዶን ምስጢር ለማናጋት ነው:: ነጮቹ እውነተኞች ቢሆኑ ኖሮ በመጀመሪያ ለሀገራቸው ሕዝብ ወንጌልን መስበክ ወገናቸው ላይ የደረሰውን የሥነ ምግባር ጉድለት ማስተካከል የተዘጋ የጸሎት ቤታቸውን መክፈት ሱቅና ቲአትር ቤት የሆነውን መመለስ በተገባቸው ነበር:: በዚህ ዓይነት ከሀገራቸው ወጥተው ወደሌላው ሀገር የሚያደርጉት ተልእኮ ወንጌል ላልደረሳቸው ወንጌልን ለማዳረስ ሳይሆን ተመሳስለው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ማንነት ለማጥፋት ነው በዚህም አካሄዳቸው

በርካታ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ምንጭ በሆኑት አብዛኛዎቹ በተለይ በሰሜኑ ክፍል በሚገኙ በአብነት ት/ቤቶችን በማዳከም

የቆሎ ተማሪዎችን ወደ ከተማ በማስኮብለል ተማሪው የሚደግመውን ዳዊት እያስጣሉ ለፍቶ እንዲያዞር የሚያደርጉበት ነው::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ሥር በሚገኙ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቤቶችን በነዚህም ት/ቤቶች የሚመለምሏቸው ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ወደ ኮሌጅም ሲገቡ ቀድሞውኑ አላማ የሌላቸውንና የቤተ ክርስቲያኒቱን በተለይ የአብነት ትምህርት የሌላቸውን ቅኔ ዜማ ወዘተ እና የመሳሰሉትን የማያውቁትን «ኢየሱስ» ብቻ ከበቂ በላይ ነው ከመጽሐፍም «መጽሐፍ ቅዱስ» ብቻ ከበቂ በላይ ነው በማሰኘት ከኮሌጆቹ እንዲኮበልሉ በማድረግ የስነ-መለኮት ደቀመዛሙርትን ያስኮበልላሉ::

የቤተ ክህነት ሠራተኞችን በጥቅማ ጥቅም ዳጎስ ያለ ገንዘብ በመስጠት የቤታቸውን ቁሳቁስ በማሟላት በውዳሴ ከንቱ በማባበልና ሥራቸውን እየለቀቁ ከነሱ ድርጅት እንዲገቡ በማድረግ በመላው ሀገራችንም ያሉትን ምዕመናን ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ስሜታቸውን በመታከክ በግጥምና በዜማቸው (ዘፈናቸው) በስብከታቸው በበራሪ ወረቀቶቻቸው ኑፋቄአቸውን በኢትዮጵያችን በቅድስት ቤተ-ክርስቲያናችን በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ::



## የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መለያ

### ድንግል

የተሐድሶ መልእክተኞች በአንድ ወቅት የግብፅ ቤተ-ክርስቲያንን አናግተዋት ነበር ይልቁንም የግብፁን ፓትርያርክ ቴዎዲስዮስ የተባለውን አሳምነው በኦርቶዶክስ ትምህርት የሌለ አዲስ ትምህርት እንዲቀበል አድርገውታል ይህም አዲሱ ትምህርት ድንግል ማርያምን በተመለከተ የኑፋቄ ትምህርት ነበር::

ትምህርቱም ድንግል ማርያም የአዳም ኃጢአት አለባት የሚልየ በርካታ የድንግል ማርያምን ክብር የሚያሳንስ ነበር ከዚህን ጊዜ ጀምሮ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ድንግል ማርያምን በተመለኩተ የተምታታ ትምህርት እንዲኖራቸው አድርጓል:: በግብፅ ቤተ-ክርስቲያን ተሐድሶዎች በተወሰነ ደረጃ ትምህርታቸው የተሳካላቸው ይመስላል:: በኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ግን እስከ አሁን ድረስ እየተነሱ ይፈርጣሉ::

የተሳካላቸው ሲመስላቸው ደግሞ እየተገነጠሉ ይወጣሉ እንጂ ቤተ-ክርስቲያኒቱን ባላችበት አስተምህሮዋንም ሆነ መዋቅሯን መለወጥና መበረዝ አልተሳካላቸውም ይህንን አለመሳካት ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን በ40 እና በ80 ቀን የተጠመቅን ክርስቲያኖች ሁሉ እምነታችንን ጠንቅቀን ስለምናውቅ ነው:: ድንግል ማርያም አምላክ አስቀድሞ ከአዳም ኀጢአት እንደጠበቃት ኦሪት ዘፍጥረት ምእራፍ ሦስት ከቁጥር

አስራ አምስት ላይ ያለውን ቃል መሰረት በማድረግ ለተሐድሶዎች መልስ እንሰጣለን

*በአንተና በሴቲቱ መካከል*

*በዘርህና በዘርዋ መካከል*

*ጠላትነትን አደርጋለሁ*

*አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ*

የሚለው የፍርድ ውሳኔ ላይ የዘፍጥረት ጸሐፊ ያስቀመጠውን መልስ መገንዘብ ያሻል::

እንደ ዘፍጥረት ጸሐፊ በምንጩ በእብራይስጥ ቋንቋ መሠረትነት ገጸ ንባቡን ሲያስነብበን **ሴቲቱ** ተብላ እዚህ ጋር የተጠቀሰችው የኢየሱስ እናት ቅድስት **ድንግል** ማርያም ስለመሆኗ ጥርጥር የለውም:: እግዚአብሔር ሴቲቱ የሚለው አዳምና ሔዋን ባጠፉ ጊዜ እንኳን ሰይጣን ላይ ፍርዱን ሲያስተላልፍ የኢየሱስ እናት **ድንግል** ማርያም ወደፊት እንደምትወለድና ከእርሷም ዘር ኢየሱስ እንደሚገኝ እየተናገረ ነው::

በዚህ ምዕራፍና ቁጥር ሴት የሚለውን የዕብራይስጥ ስርወቃል ልንመረምረው የግድ ነው በአማርኛ ሴት ተብሎ ተተርጉሞ የምናገኘው የዕብረይስጥ ቃል ሦስት ዓይነት ሴቶችን የሚገልጽ ስርወ ቃል አለው::

1. አልማ የሚለው ቃል ወንድ የማታውቅ ወይም ያላገባች ድንግል ሴትን ያሳያል



2. ነርሐ ማለት ደግሞ ያገባችም ያላገባችም ልትሆን የምትችል ድንግል የሆነች ወይም ያልሆነች ሴት ልትጠራበት የምትችል ቃል ነው::
3. ቤቱላህ ደግሞ ትልቅ ወይም ትንሽ ልትሆን ትችላለች ዳሩ ግን ድንግል ሴትን ይገልጻል::

የእነዚህን ቃላት አተረጓጉጎም ይዘን በመጀመሪያ በኦሪት ዘፍጥረት ጸሐፊ ምዕራፍ ሦስት ከቁጥር 15 በአንተና በሴቲቱ መካከል በሚለው አገላለጽ ሴቲቱ ብሎ የእብራይስጥ ቃሉን የሚጠቀመው ድንግል የሆነች ወይም ያልሆነች በሚለው በቤቱላህ ቃል ስለተነገረ **ድንግል** ማርያምን የሚያነሳ አይደለም ብለው ተሐድሶዎች ሙግት ያነሳሉ ነገር ግን እንደ ሙሴ የስነ መለኮት እስተምህሮ የአዳም ሚስት ሔዋን በኤደን ገነት እያለች ሴት ትባል ነበር ነገር ግን ሩካቤ ሥጋ በኤደን ገነት እያለች አልፈጸመችም እንደዚሁ ሁሉ ቅድስት **ድንግል** ማርያም ዮሴፍ ጠባቂዋ በነበረ ጊዜ ሴት ትባልና በዚህ ስም ትጠራ ነበር ይሄም ንጽጽራዊ ትምህርተ መለኮትን ሲያስተምር ወንድ አጠገቧ እያለ ነገር ግን የእርሷ ዘር ብቻ ዓለምን ለማዳን እንደተፈለገ ሙሴ በንጽጽር አስቀምጦታል እንዲህ ንጽጽራዊ የስነ መለኮት አስተምህሮ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ግን **ድንግል** ቅድስት ማርያምን ወክለው የሚቀመጠው የእብራይስጥ ቃል አልማ የሚለውን

እና ዘላለማዊ ድንግል ሴት ተብሎ ሊተረጎም የሚችለውን ቃል ብቻ ነው።

**ድንግል** [አልማ]

የትንቢተ ኢሳይያስ ጽሐፊና ነቢዩ ኢሳይያስ

እነሆ ድንግል[አልማ] ትጸንሳለች ሲል [ኢሳ.7÷14] የምትጸንው ሴት በዕብራይስጥ ቋንቋ አልማ በሚለው ዘላለማዊ ድንግልናን በሚገልጸው ቃል የተቀመጠ ነው። በዚህም ምክንያት እዚህ ጋር በትንቢቱ በቀጥታ ሴት በሚለው ስሟ እየጠራት ያለው ዘላለማዊ ድንግልና ያላት የኢየሱስን እናት **ድንግል**ማርያምን ብቻ ነው ሊጠቅሳት የሚችለው ይኸውም ቃል እርሷን እንደሚመለከት የማቴዎስ ወንጌል ጸሐፊ መልእክ ዮሴፍን ባረጋጋበት አንቀጽ ይህንን የኢሳይያስን ትንቢት ጠቅሶ አረጋግቶታል።

በሌላኛው አስተምህሮ ደግሞ ነቢዩ ሚክያስ ስለዚህ ቃል እንዲህ በማለት በትንቢቱ ተጽፎ ይገኛል።[ሚክ.5÷2]

አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ
በእስራኤል ላይ ገዢ የሚሆን
ይወጣልኛል ስለዚህ <u>ወላጂቱ</u>
እስክምትወልድበት ጊዜ ድረስ

አሳልፎ ይሰጣቸዋል ሲል ወላጂቱ የሚለውን ለመግለጽ የሚያገለግው ቃሉ በእብራይስጥ ቤቱላህ በሚል ተቀምጧል።



ይሄ ደግሞ እናትም የሆነች ነገር ግን ድንግልናም ያላትን ሴት የሚወክል ቃል ሲሆን በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ከቁጥር 15 ላይ ካለው ቃል ጋር ይዛመዳል ይህ ማለት የቅድስት **ድንግል** ማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና ለመግለጽ አልማ የሚለውን ቃል እየተጠቀሙ ሲሆን ነገር ግን የቅድስት **ድንግል** ማርያምን እናትነትም ድንግልናም ለመግለጽ ደግሞ ቤቱላህ.የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ ዳሩ ግን ነርሐ.የሚለውንና ሌሎችን የዚህን ዓለም ሴቶች የሚወክለውን ቃል ለቅድስት **ድንግል** ማርያም ተጠቅሶ አይገኝም።

ከዚህ መረጃ ደግሞ ሴቲቱ የሚለው ቃል ሔዋን በኤደን ገነት ሳለች የተጠራችበት ቃል ስለሆነ ቅድስት **ድንግል** ማርያምም አሁን ድረስ በኤደን ገነት ሳለች ሴት የሚለውን ስም ያወጣላት ፈጣሪ እስከሆነ ድረስ ቅድስት **ድንግል** ማርያምም ዛሬ ድረስ ለንጽሕናዋና ለድንግልናዋ መጠርያ ስለሆነ ሴት[አልማ] ተብላ ትጠራለች ሴት የሚለው ስም ድንግልናን ንጽሕናን የሚገልጽ ስለሆነ ሔዋን ግን ከኤደን ገነት ስለተባረረች ሴት[አልማ] በሚለው ስም እንድትጠራ አልተፈቀደላትም በዚህ ምክንያት አዳም ለሚስቱ «ሔዋን» ብሎ ስም አወጣላት ይላል።

ሴት በሚለውና በሔዋን በሚሉት ስሞች መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ የዘፍጥረት ጸሐፊ ሙሴ አዳም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣለት ሲል እያስተማረን ያለው አስተምህሮ አለ ይኸውም አዳም ለሚስቱ በኤደን ገነት እያለ ስም አላወጣላትም ምክንያቱም ሔዋን በኤደን ስትኖር ሴት[አልማ] ተብላ በመጠሪያነት ስትጠራ የነበረው ንጽሕት ቅድስት ድንግል ወንድ የማታውቅ ስለነበር ብቻ ነው::

ከገነት ከተባረረች ቡኋላ ግን ሴት የማትባለው የአዳም ሚስት በመሆኗና ሩካቤን ከአዳም ጋር በመፈጸሟ ንጽሕናዋና ድንግልናዋ ስለቀረ ሴት[አልማ] ተብላ መጠራት የለባትም ስለዚህ ለኃጢአቷና ለማንነቷ ተስማሚ የሆነ ስም ሔዋን ብሎ አወጣለት::

በመሆኑም በአንተና በሴቱቱ[አልማ] ዘር ተብሎ የተነገረው የሴቲቱ ዘር ፈጽሞ የሔዋን ሊሆን አይችልም በቀጥታ ሴቲቱ እያለ ፈጣሪ እየተናገረ ያለው በኋላ ዘመን ጊዜው ሲደርስ የሚወለደው ከቅድስት **ድንግል** ማርያም ስለሆነ የቅድስት ማርያምን ስም በቀጥታ እየተጠራ መሆኑን ሙሴ እየነገረን ነው::



እንደ ሙሴ አስተምህሮ በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነት አኖራለሁ በሚለው የፈጣሪ አገላለጽ ጠላትነት የሚለው ጊዜአዊ ጠላትነትን የሚያሳይ ሳይሆን ዘላለማዊ ጠላትነትን የሚያሳይ ቃል ነው ያ ዘላለማዊና የማያቋርጥ ጠላትነት ደግሞ በሔዋንና በእባብ መካከል ሊኖር ፈጽሞ አይችልም ሔዋን ንስሐ እንኳ ብትገባ ሰይጣንን የመርታት አቅም በፍጹም እንደሌላት ሙሴ እየነገረን ነው ሙሴ በድጋሚ በአንተና በሴቱቱ[አልማ] ዘር በሚለው አገላለጹ ደግሞ የሰይጣንን ራስ የሚቀጠቅጠው የሴቲቱ ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ ልጇ እንደሆነና እርሷም ሴት በሚል መጠርያ የተነገረላት የቅድስት**ድንግል** ማርያም ስም እንደሆነ ፈጣሪ ጊዜው ሲደርስ ከእርሷ የሚወለደውን ልጇን እንደሚልክ ሙሴ የዚህን ትንቢት መፈጸሚያ ጊዜ ቀጥሮ መነሻውን እየነገረን ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንን እውነት ስለተረዳው
የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት (ንጽሕት ድንግል) የተወለደውን ልጁን ላከ ይላል ጳውሎስ በዚህ አገላለጽ የኢየሱስ እናት **ድንግል**ማርያም ሙሴም በአንተና በሴቲቱ መካከል በማለት የጊዜውን መነሻ እንዳሳወቀ አሁን ደግሞ ጊዜው ተፈጽሞ ከዚሁች ሴት እንደተወለደ ሴት የሚለውን የ**ድንግል**ማርያምን ስም ተጠቅሟል::

ሐዋርያው ጵውሎስ በነበረበት ዘመን ስሟን በሚገባ **ድንግል** ማርያም መባሏን ያውቃል:: ይልቁንም ሐዋርያው ጳውሎስ እንኳን የሚያውቃቸውን ሰው ስም ይቅርና የሙሴን ሙሉ ሐሳብና ማንነት የአጻጻፍ ስልት ስለሚያውቅ::

ሙሴ በጽሑፍ የፈርኦንን ጠንቋዮች ስም ባይጠቅስም ጳውሎስ የእያኔስና እያንበሬስን እንደሚባሉ የፈርዖንን ጠንቋዮች ስም ይጠቅሳል ሐዋርያው ጳውሎስ በእጅጉ የሙሴን አስተምህሮ ጠንቅቆ ያውቃል በመሆኑም ሙሴ በአንተና በሴቲቱ .መካከል ጠላትነትን እኖራለሁ የሚለውን አገላለጽ በእጅጉ ስለተረዳው ሴቲቱ የተባለችውም **ድንግል**ማርያም እንደሆነች ያውቃል:: **ድንግል** ማርያም ብሎ ከሚለው ይልቅ ጳውሎስ ሴቲቱ የሚለውን እግዚአብሔር ቀን የቀጠረበትን የ**ድንግል** ማርያምን ስም መርጧል:: ይህም ሴት የሚለው ቃል[አልማ] የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል የሚተረጉመው ሲሆን ጌን.የሚለውን የግሪክኛ ቃል ሲተረጎመው ሌሎችን ሴቶች አይጠቅስም የቅድስት **ድንግል** ማርያም መጠሪያ ሆኖ ግን ያገለግላል ስለሆነም ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ጌን የሚለውን የግሪክኛ ቃል ሲጠቀም የሙሴን እሳቤ እየመሰከረ ነው በዚህም አገላለጽ ሴት ሲል ንጽሕት ቅድስት ድንግል ወንድ የማታውቅ የሚለውን ቀመር እንደያዘ እያስረዳን ነው::



የኢየሱስ እናት **ድንግል** ማርያም እራሷ የነቢያትን ትንቢት የመተርጎም ከበቂ በላይ ዕውቀት ስለነበራት ከመልአኩ ከገብርኤል ጋር በነበራት ውይይት ከዚህ በፊት ሙሴ ሴቲቱ ያላት እርሷን መሆንዋንና የአዳም ኃጢአት እርግማንና ቁጣ ያልነካት መሆኗ በመግለጽ ፈጣሪ አብርሃምን በዘርህ አሕዛብ ይባረካሉ የሚለውን ትንቢት ስትተረጉመው መልአኩን በማይነገር ጥበብ በአዳም በኩል አድርጋ አብርሃም አብራክ ውስጥ እርሷን በአብርሃም አብራክ ሊያገለግል የዘላለሙ ካህን መልከጸዴቅ ተገልጾ ይህ ብሥራት ፈጣሪ ለአብርሃምና ለዘሩ የሰጠውን ቃል ኪዳን ለመፈጸምና ለመጠበቅ እኔ ሴቲቱን ተጠቀመ ብላ ምስጋናዋን ዘግታለች::

ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስም እናቱ ቅድስት **ድንግል** ማርያም በገሊላ ቃና ሰርግ ቤት የወይኑን ማለቅ በነገረችውና አንዳች ነገር እንዲያደርግ ባዘዘችው ጊዜ እርሱ ቀድሞ የነበረውን የኦሪት ዘፍጥረትን አስተምህሮ መሠረት አድርጎ እናቱን አንቺ ሴት ብሎ ንጽሕት ቅድስት ድንግል ብሎ የአይሁድ ሊቃውንትና የሙሴ መጽሐፍት ተርጓሚዎች ባሉበት ሰበካት::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር ይቆየን

http://www.andadirgen.blogspot.com/

አንድ አድርገን

ሌሎች ስለተሐድሶ እና መናፍቃን እንቅስቃሴ የተፃፉ መፅሀፍትን ለማውጣት በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡

‹‹የምንፈራው እውነት የለም››

